የሲያትል ከተማ የመንደር አስተዳደር

ፒ-ፓች (P-PATCH) የማህበረሰብ አትክልት የመትከል ፕሮግራም

ፒ-ፓች (P-Patch) የማህበረሰብ አትክልት የመትከል ፕሮግራም በሲያትል አካባቢዎች በሚገኙ ክፍት ቦታዎች የሚካሄድ የማህበረሰብ ፕሮግራም ነው። አትክልተኞች በተናጠል እና በህብረት ላይ ከማዳበሪያ ነጻ የሆነ ምግብ፣ አበባዎች፣ ፍራፍሬዎች እና የቅመም ቅጠሎች ለመትከል ትናንሽ የአትክልት መደቦች ይጠቀማሉ።

ሕዝቡ እንዲደሰትባቸው የአትክልት ቦታዎቹ ለሕዝብ ክፍት ናቸው። እያንዳንዱ የአትክልት ቦታ ልዩ ነው እንዲሁም የተለያዩ የፒክኒክ ቦታዎች፣ ወንበሮች፣ ሰነ-ጥበብ፣ የአበባ ሰፍራዎች፣ የመማሪያ ምልክቶች፣ የመቋ ቋ ሚያ ሰርቶ ማሳያዎች እና የልጆች የአትክልት ቦታዎችን ሊያካትት ይችላል።

የፕሮግራሙ ዝርዝሮች

የፒ-ፓች (P-Patch) የማህበረሰብ አትክልት የመትከል ፕሮግራም በሲያትል ከተማ የመንደር አስተዳደር የሚካሄድ ነው። እስከ ታህሳስ 2016 ድረስ 90 ፒ-ፓች (P-Patch) የማህበረሰብ የአትክልት ቦታዎች፣ 3055 የአትክልት መደቦች እና 6800 አትክልተኞች ይገኛሉ።

የፒ-ፓች (P-Patch) አትክልት ቦታዎች በርካታ ታሪክ ያላቸው እና በጣም የተለያዩ ፍላጎቶችን የሚያሟሉ ናቸው። የመጀመሪያው የአትክልት ቦታ የፒካርዶ እርሻ (Picardo Farm) በ1973 በማህበረሰቡ የነዋሪዎች ቡድን እና በሲያትል ከተማ ተቋቋመ። የአትክልት ቦታዎቹ በተለያዩ የከተማው መምሪያዎች ስር ባሉ በሕዝብ ንብረቶች እና ሌሎች የሕዝብ እና የግል ባለንብረቶች በተያዙ የሕዝብ ንብረቶች ላይ የተቋቋሙ ናቸው። የአትክልት ቦታዎቹ ከትንሽ እስከ ትልቅ የተለያዩ ናቸው እንዲሁም ከማህበር መሰል (የጋራ የአትክልት መደቦች) እስከ ትላልቅ የገበያ እርሻ ቦታዎች (ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ገበሬዎች ለሽያጭ የሚቀርቡ ምግቦች) ናቸው።

አስደሳች የሆኑ እውነታዎች

ለረዘመ ጊዜ የቆየ፡- ፒካርዶ (2.5 ኤከር)

የተለቀ ቦታ፡- ቲስልስ (Thistle) (3+ኤከር)

ከፍ ያለ መደብ ያላቸው የቦታዎች # ፡- 18

አዲሱ ቦታ፡- Troll’s Knoll

ከሁሉም ያነሰ ቦታ፡- ኢዳሚያ (IdaMia) (700 ስኩዌር ጫማ)

የገበያ የእርሻ #፡- 3

Seattle Neighborhoods

P-PATCH COMMUNITY GARDENING PROGRAM

የሲያትል ከተማ የመንደር አስተዳደር
ፒ-ፓች (P-PATCH) የማህበረሰብ አትክልት የመትከል ፕሮግራም

ተጨማሪ የፕሮግራሙ እውነታዎች

በትብብር የሚገኝ ስኬት

ከሰራተኞቻችን ስራ በተጨማሪ የፒ-ፓች (P-Patch) ማህበረሰብ የአትክልት ቦታዎች በበርካታ ድርጅቶች እና በራሳቸው በአትክልተኞቹ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ

- Solid Ground's Lettuce Link (ሶሊድ ግራውንድስ ሌተስ ሊንክ)
- GROW (ግሮው)
- Seattle Tilth (ሲያትል ቲልዝ)
- Seattle Housing Authority (የሲያትል የቤቶች ባለስልጣን)
- 6800+ በዓመት 42,000 ሰዓት በፈቃደኝነት የሚሰሩ አትክልተኞች

ፒ-ፓች(P-PATCH) የማህበረሰብ የአትክልት ቦታ ፍላጎት

ያለው ፍላጎት ከፍተኛ ስለሆነ የማብቀል ችሎታ ለማሳደግ እንዲሁም ሌላ የማህበረሰብ አትክልት የመትከል ጥረቶችን ለመደገፍ ሰራተኞች እንደሚከትለው እያሰሩ ነው፡-

- ፍላጎት ያላቸው የሰዎች ዝርዝር 1,000+ (እስከ ታህሳስ 2016 ድረስ)።
- ለግለሰብ የአትክልት ቦታዎች የመጠበቂያ ጊዜ ከ3 ወር እስከ 4 ዓመት።
- በአጠቃላይ በሁሉም ፕሮግራም በዓመት 25% ይቀያየራሉ።

ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው እና የአናሳ ህዝቦች ፕሮግራሞች

ካሉን መሰረታዊ እምነቶች ውስጥ፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውንና ተገቢ ውክልና ያላገኙ ማህበረሰቦችን መደገፍ ነው። እንደ አንድ ምሳሌ ሊጠቀስ የሚችለው የ Market Garden Program ነው። በ Seattle Housing Authority ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውና ኢሚግራንት ቤተሰቦች፣ የጓሮ አታክልት ተክለው የአታክልት ምርቶችን በአካባቢው ለሚኖሩ ሰዎች ይሸጣሉ። በ 2016 ውስጥ፣ አምስት ባህሎችን የሚወክሉ፣ 14 የጓሮ አትክልተኞች ለእርሻ ምርት መሸጫ መደቦችና በማህበረሰብ ለሚደገፍ የግብርና ፕሮግራም (CSA) የአታክልት ምርቶችን ለማቅረብ ተባብረዋል።

ፕሮግራሙ የገንዘብ ድጋፍም ይሰጣል። በ 2016፤ ከ73 ፒ-ፓች (P-Patch) የአትክልት ቦታዎች ከ550 በላይ የሚሆኑ ቤተሰቦች እርዳታ አግኝተዋል፡፡

የአትክልት ቦታ ክፍያዎች

የአትክልት መደቦች የተለያየ መጠን አላቸው፡-
10' x 10' – $43
10' x 20' – $57
10' x 40' – $85

የአትክልት መደብ ክፍያውን መክፈል ለማይችሉ የገንዘብ እርዳታ አለ።

ከዓመቱ ክፍያ በተጨማሪ የፒ-ፓች (P-Patch) የህዝብ ቦታዎችን ጠብቆ ለማቆየት ስምንት ሰዓት የፈቃደኛነት ጊዜ መስጠትን ይጠይቃል።

የአትክልተኞች የምደገፈያ የምግብ ባንኮች

- 53 የአትክልት ቦታዎች የመሰብሰቢያ ፕሮግራሞች አሉዋቸው ወይም የተለየ "የልገሳ የአትክልት ቦታ" ለምግብ ባንኮች እና ለትኩስ ምግብ ፕሮግራሞች የሚሆኑ የሚበቅሉባቸው መደብ አሉዋቸው።
- በ2016 አትክልተኞቹ ከ24,178 ፓውንድ በላይ የሚሆኑ ምርቶችን ለግሰዋል።

የኢድራሻ መረጃዎች

ፒ-ፓች (P-Patch) የማህበረሰብ አትክልት የመትከል ፕሮግራም
የሲያትል ከተማ የመንደር አስተዳደር

ስልክ፡- (206) 684-0264
ኢሜይል፡- p-patch.don@seattle.gov
ድረ ገጽ፡- www.seattle.gov/neighborhoods/ppatch/